## ሆዴ ልመድ

**4 5 131 /፪/**

**31513 242**

ሆዴ ልመድ
የለህምና ዘመድ

## በጌቴ ሴማኔ

**4 2 3 2 2 4 5 4 2 2 2 2 /፪/**

**4 2 3 115 113 2 2 4 5 4 2 2 2 2**

በጌቴ ሴማኔ በአትክልቱ ቦታ /፪/
ለእኛ ሲል ጌታችን በዓለም ተንገላታ /፪/

አዳምና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት /፪/
ለእኛም ነበረብን የዘላለም ሞት /፪/

መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ /፪/
ይገርፉት ነበረ ሁሉም በየተራ /፪/

ድንግል አልቻለችም ዕንባዋን ልትገታ /፪/
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ /፪/

በኣምላክነቱ ሳይፈርድባቸው /፪/
እንዲህ ሲል ጸለየ አባት ሆይ ማራቸው /፪/

በረቂቅ ስልጣኑ ሁሉን የፈጠረ /፪/
በሰዎች ተገርፎ ሞተ ተቀበረ /፪/

ፍቅሩን የገለጸው ተወልዶ በሥጋ /፪/
ኢየሱስ ጌታ ነው አልፋና ዖሜጋ /፪/

## በመስቀል ተሰቅሎ

**4 2 3 2 2 4 5 4 2 2 2 2**

**4 2 3 2 2 4 5 4 2 2 2 2**

**4 2 3 115 113 2 2 4 5 4 2 2 2 2**

በመስቀል ተሰቅሎ እንዲያ እየቃተተ
ዓለምን ለማዳን የማይሞተው ሞተ /፪/

ከሞት ሊታደገን በመጣልን ፈጥኖ
መስቀል አሸከሙት ውለታው ይህ ሆኖ /፪/

መከራውን ሳስብ ሳስታውስ ቀኑን
ይቆስላል ይደማል ልቤ በኀዘን /፪/

መች ለራሱ ነበር የሁኑ መከራ
መስቀል ተሸክሞ የወጣው ተራራ /፪/

ሲያጎርሱት የሚነክስ ሰው ክፉ ነውና
እውሩን ሲያበራ ጎባጣን ቢያቀና
ጌታዬን ሰቀሉት አይሁድ ጨከኑና /፪/

ምነው አያሳዝን የአይሁድ ክፋት
የዝናቡን ጌታ ውሃ ሲነፍጉት /፪/

በተንኮል በኃጢአት ቀሩ እንደሰከሩ
ሙታን ከመቃብር ተነስተው ሲያስተምሩ /፪/

እናታችን ሔዋን ወዮ በይ አልቅሺ
ያንቺን ህመም ታሞ ከሞት ሊያድንሽ
የህያዋን ጌታ ተሰቀለልሽ /፪/

አየጉድ አየጉድ ዓለም የኋላሽ
መድኃኒት ክርስቶስ በግፉ ሞተብሽ /፪/

በመስቀል ተሰቅሎ ሥጋውን ሲቆርስ
በችንካር ተወግቶ ደሙንም ሲያፈስ
ዋለች በመከራ ድንግል ስታለቅስ /፪/

ሰውነትሽ ራደ ኀዘን ከበበሽ
ሥቃይ መከራውም ዳግም ጸናብሽ
ተሰቅሎ ሥታይ አንድዬ ልጅሽ /፪/

ቢፈስም እንባዬ ሆኖ መንታ መንታ
መች ዋጋ ይሆናል ለአንዷቱ ጠብታ
ላለቀሽው ለቅሶ ድንግል የዛን ለታ እናት የዛን ለታ

ባለቀሽው ለቅሶ በልጅሽ ህመም
ከኃጢአት ነጻሁኝ ዳንኩኝ ከገሀነም /፪/

## ኧረ ስማኝ ፈጣሪ

**423 224 542 222**
**423 224 542 222**
**423 115 113 224 542 222**

ኧረ ስማኝ አምላኬ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ /፪/
አላገኝምና ያለአንተ መሃሪ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ /፪/

አድነኝ ጌታዬ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ሁሉንም ትተህ " "
ይቅር በለኝ አምላክ " "
በደሌን ንቀህ " "
ዘወትር ነውና የማስቀይምህ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ

በደኔን አውቄ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ወዳንተ ስጠይቅ " "
በሰራሁት ኃጢአት " "
መንፈሴ ሲጨነቅ " "
ይቅር በለኝ እንጂ ምህረትን አታርቅ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ

እያውቅሁ አጥፍቼ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
እኔም ብበድልህ " "
ከሥጋ ገበያ " "
ውዬ ባስቸግር " "
እስኪ አድነኝ አንተ የምህረት አምላክ ነህ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ

እስኪ ዛሬ ይብቃ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ልዙር ወደ ነፍሴ " "
መፈጠሬ ይግባኝ " "
በአርአያ ሥላሴ " "
ተቀበለኝ አምላክ ልጀምር ውዳሴ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ

ለሥጋ እያደላሁ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ብዙ አጠፋሁኝ " "
አውቄ እንዳለወቅሁ " "
ቃልህንም ሻርኩኝ " "
አምላክ ይቅር በለኝ አሁን ፀፀተኝ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ

እንድታማልደኝ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ድንግልን ጠይቄ " "
አለቅሳለሁ እንጂ " "
ከፊትህ ወድቄ " "
የትስ እደርሳለሁ ከመንፈስህ ርቄ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ

ይቅር በለኝ ብዬ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ወዳንተ ሣለቅስ " "
የእንባ ዘለላ " "
በጉንጮቼ ሲፈስ " "
ምህረትን ነው እንጂ " "
በደሌን አታስታውስ " "
ፊትህን ወደእኔ እባክህን መልስ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ

## ድንግል ስልሽ

**22 4 2315 4 542 22 4 2313111**
**1545 13 113 15 4 22 4 23122**
**(5422 22)**
**542 542**

*ድንግል ስልሽ ማርያም ስልሽ*
*እንደ በላኤ ሰብ ይጋርደኝ ጥላሽ ድንግል ስልሽ*

በጭንቅ ውስጥ ሆኜ ከቦኝ መከራ
የአምላክ እናት ስምሽን ስጠራ
ታማልጅኝ ዘንድ ልቦናሽ ይራራ /፪/

ጭንቁ በረታ ሀዘን ከበበኝ
ኃጢአቴ በዛ ተስፋ ቢስ ሆንኩኝ
ድንግል እመቤቴ ምልጃሽ አይለየኝ /፪/

ልጅሽ በሰጠሽ ቃል ኪዳንሽ
ተግተሽ ዘወትር እያማለድሽ
የሰውን ልጅ ሁሉ ታስምሪዋለሽ /፪/

ስምሽ እንደ ማር እየጣፈጠኝ
ደግነትሽም እየመሰጠኝ
ሁሌ እዘምራለሁ ልቤን ደስ እያለኝ /፪/

እምነቴ ሳስቶ ጽድቅም ባልሠራ
እመቤቴ ሆይ ነፍሴን አደራ
አስታርቀሽ አኑሪያት ከቅዱሳን ጋራ /፪/

ድንግል በሃና በእናትሽ
በኢያቄምም በአባትሽ
ተማጽኜሻለሁ ልቁም በፊትሽ /፪/

አንቺን ስጠራ ልቤ ይረካል
ሀዘን ርቆ ሰላም ይተካል
ለሀዘንተኞች ተስፋ ከቶ እንዳንቺ የታል / ፪/

## አባታችን ሆይ

**4 2 4 5 3 1 3 1 5 4 2 3 3 1 2 4 5**
**4 2 4 5 3 1 3 1 5 4 4 2 2 2 2**

አባታችን በሰማያት ላይ ያለህ
ተለይቶ ይመስገን ቅዱስ ስምህ

መንግሥትህን የምንፈልጋት ከጥንቱ
በልጅነት ትመጣ ትሰጠን አቤቱ

ፈቃድህም ይህ እንዲደረግ ይሁን
በሰማይ ሞተን ተነስተን ከደይን

እድንኖር ምሥጋናህ ምግብ ሆኖን
ዛሬም በምድር በሥጋ ሕይወት ሳለን

ምግባችንን በየዕለቱ አውቀህ ስጠን
ይቅር በለን የበደልንህን ነገር

ወንድማችን የበደለንም ቢኖር
እንደአቅማችን እኛም እንድንል ይቅር

ከገሃነም ከክፉ ሁሉ መዓት
አትጣለን አድነን እንጂ ከሞት

ይህችን መንግሥት የማያገኛት ኀልፈት
ጌትነትም ከሀሊነትም ክብርም

ናችውና የአንተ ገንዘቦች ሁሉም
ለዓለም ወለዓለም ዓለም አሜን

የተላከው ቅዱስ ገብርኤል ከጌታ
ሰላም ለኪ ብሎ በሰጠሽ ሰላምታ

እኔ ባርያሽ ልብሴን ስታጠቅ ስፈታ
ሰላም ልልሽ ይገባኛል ጠዋት ማታ

ማርያም ሆይ እመቤቴ ሆይ ድንግል
በሥጋም በሕሊናሽም ድንግል

የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ድንግል
እንዳለሽ ቅዱስ ገብርኤል ሰላም

ሰላም ለኪ እንደርሱ ሁሉ እኔም
የሌለብሽ የነፍስ የሥጋ መርገም

ብሩክ ነው የማሕፀንሽ ፍሬም
እንደቀድሞው ቡሩክ አምላክ ነው ዛሬም

እግዚአብሔር ወልድ በመጣ ጊዜ ለካሳ
እንበለ ዘር እንደ ንብና እንደ ዓሣ

ከነፍስሽ ነፍስ ከሥጋሽ ሥጋሽ ቢነሳ
ደስ ያለሽ ወይ ጸጋን አግኝተሽ ከጌታ

ደስ ይበልሽ በማቀርብልሽ ሰላምታ
ለምኚልን ሳትሰለቺ ጠዋት ማታ

ውድ ልጅሽ እንዲያደርግልን ይቅርታ
ይቅር ብሎ ኃጢአታችንን ሁሉን

እንዲያድነን በአንቺ ተማፅነን አለን
ለዓለም ወለዓለም ዓለም አሜን

## ስለ ሥነ ፍጥረት

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሐዱ አምላክ ብዬ ሰላምታ ላድርስ

ለፈጠርከኝ ለሰማዩ ንጉሥ
እንዴት አለህ መጥቼ እስካይህ ድረስ

ያስደንቃል ያኗኗራቸው የጥንቱ
የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ የሦስቱ

ሦስት ናቸው በአካል በገጽ በስም
አንድ ናቸው በትእዛዝ በክብር ፍፁም

ሥላሦችም እም ቅድመ ዓለም ሲኖሩ
ዓለም መፍጠር እሁድ በሰርክ ጀመሩ

ያን ጊዜውን ሰባት ፈጠሩ በቅጽበት
አስቀድመው ሰማይና ምድርን በፊት

አራተኛ መላዕክትና ጽልመት
ሰባተኛ ማይና ነፋስ እሳት

በአርምሞ ይህን ሁሉ ፈጥረው
ተናገሩ ለይኩን ብርሃን ብለው

ሰኞ ጠዋት ውኃን ከፈሉት ከሦስት
አንደኛውን አዘቅት አረጉት ከምድር

ሁለቱን ሰማይ አረጉት ጠፈር
ማከሰኞም አብቅይ አሏት ምድርን

አበቀለች ሳር ቅጠሉን እህሉን
ረብዕም ረቂቅ ሥራን ሲሰሩ

ከዋክብትን ፀሐይ ጨረቃን ፈጠሩ
ሐሙስም አልተውምና መፍጠር

የሚበሩ ክንፍ ያላቸውን ነገር
የማይበሩ የሚሄዱትን በእግር

በባህርም ዓሣ ጉማሬ ሳይቀር
ዓርብ ጠዋት አዳምን የኛን አባት

ንግበር ብለው በነሱ አምሳል ሠሩት
በሣልሰት ሔዋንን ፈጥረው ሰጡት

ትርዳህ ብለው ብቻውን ሆኖ ቢያዩት
የሥላሴዎች የፍጥረታቸው ፍፃሜ

በሰባት ቀን ዳርቻ ሆነች ቅዳሜ
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

ለዓለም እስከ ዘላለም ድረስ

## ስለ ልደት

ድንግልም በምትወልድበት ወራት
በሮም ንጉስ በአውግስጦስ ቄሳር መንግስት

ሰው ሁሉ ግብር ሊቆጠር ታዘዘ
ዮሴፍም ድንግልን ይዞ ተጓዘ

ከገሊላ ከነበረበት መንደር
ቤተልሔም ወደምትባል ሀገር

ከኤፍራታ ይወጣል ብሎ ንጉሥ
ሚክያስ የተናገራረው ሊደርስ

ሳታፋልስ የወላዶችን ሥርዓት
በታኅሣሥ በሃያ ዘጠኝ ዕለት

ከዚያዉ ሳሉ የምትወልድበት ቢደርስ
ተወለደ ድንግልናዋን ሳይጥስ

ቤት ባይኖራት መጥታለችና ከሩቅ
ከበረት ጠቀለለችው በጨርቅ

ሊፈጸም የኢሳይያስ ነገሩ
እንስሳትም ትንፋሻቸውን ገበሩ

ከዚያ ቦታ ከብት ጠባቂዎች ነበሩ
ያዩ ነበር ካሉበት ቦታ ድረስ

የብርሃን ጎርፍ ከቤተልሔም ሲፈስ
እረኞቹም የብርሃኑን ጎርፍ አይተው

እጅግ ፈሩ ምን ነገር ነው በለው
መልአኩም ፍርሐታቸውን አርቆ

ነገራቸው ተድላ ደስታውን አድንቆ
ልዑል አምላክ ለአዳም ልጅ በሎ ተዋርዶ

ለድንግል በዳዊት ባሕርይ ተወልዶ
ጨርቅ ለብሶ ከበረት መሓል ተጥሎ

አለላችሁ ሄዳችሁ እዩት በቶሎ
እንዲህ ብሎ ሲናገራቸው በዜና

ከእርሱ ጋራ ብዙ መላዕክት መጡና
አቀረቡ ከእረኞች ጋር ምስጋና

ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

## ስለ ዳግም ምፅዓት

እንዲህ አርገን ሥራውን ሁሉ አምነን
እናምናለን ዳግም ይመጣል ብለን

ነገር ግን ዳግም ይመጣል ሰላልን
ከፃድቃን ከመላእክትም ቢሆን

የሚያውቅ የለም የሚመጣበት ቀኑን
ባላወቅነው ባልመረመርነው ሰዓት

ግሩም ሆኖ ይመጣን እንጂ ድንገት
መጀመሪያ የአዋጅ ነጋሪት ሲመታ

ከያለበት ይሰበሰባል በአንድ አፍታ
አጥንታችን ትቢያ የሆነው አፈር

ጅብ የበላው የተበተነው ከዱር
የራስ ፀጉር የእግር ጥፍራችን ሳይቀር

ተሳስቶ የአንዱ ወደ አንዱ ሳይዞር
በየራሱ ይሰበሰባል ሁሉም

ይመታል የአዋጅ ነጋሪት ዳግም
ነፍስ የሌለው በድን ይሆናል ፍፁም

በሶስተኛው የአዋጅ ነጋሪት ሲመታ
ይነሳሉ መልካም የሠሩ በዕልልታ

የብርሃን ልብስ የብርሃን ቀሚስ ለብሰው
እንደ ፀሐይ እንደ ጨረቃ ደምቀው

እግዚአብሔርን ፈጣሪያቸውን መሰለው
ይሰሙና በቀኙ ቆመው ፍርድን

ከማያልፈው ተድላ ደሰታ በቀር
ጠግቦ ቁንጣን ተርቦ ስስት ሳይኖር

ገብቶ መውጣት አግኝቶ ማጣት ችጋር
የሌለባት ደገኛይቱን ሀገር

ይወርሳሉ መልካም የሠሩ በምድር
ኃጥአንም እጅግ ከጭራ ቀጥነው

መልካቸውም እጅግ ከቁራ ጠቁረው
ከላይ ከታች የጨለም ልብስ ለብሰው

ዲያብሎስን ለአለቃቸውን መስለው
ይሰሙና በግራ በኩል ቆመው

በመንቀጥቀጥ የሚፈርደውን ሰምተው
ከልቅሶና ጥርስ ማፋጨት በቀር

ተዳላ ደስታ የሌለባትን ሀገር
ይወርሳሉ ክፉ የሠሩ በምድር

እንዲህ አርገው መጻሕፍት ሁሉ እንዳሉ
በየሥራው ይከፍለዋል ለሁሉ

ሰብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

## ሰላም ለኪ

ሰላም ለኪ ማርያም ድንግል ንጽሕት /፫/
ያቺን ርግብ ያቺን ወለላ ፍጥረት

በበገና እስኪ ላመስግናት ጥቂት
የአምላክ እናት የሰማይ የምድር ፈጣሪ

የእርሷ አዝማሪ ዕዝራና ዳዊት በባህሪ
ቃል ኪዳኗ የማይፈርስባት ነዋሪ

እልፍ አዕላፍ መላእክት አሉዋት ነባሪ
ያገልግሉሽ ብሎ የሰጣት ፈጥሪ

እኒያን ይዛ ፍጥረት ዓለሙን መካሪ
ወለላዊት ቤዛዊት ዓለም ብፅዕት

ከወተት ወዳሴሽ ጥዑም በእውነት
ከወለላ ተአምርሽ ጥዑም ሲበላ

የብርሃን ዘውድ የብርሃን አክሊል ደፍተሽ
ድረሽልን በሰለገላ ሆነሽ

ይሸሻሉ ኢጋንንት አንቺን ሲያዩሽ
ቤተመቅደስ ስታገለግል ስትሠራ

ነይ ውጪ አሏት ሊቃውንት መክረው በሴራ
ተመቅኝተው ምናምን ኃጢአት ሳትሠራ

እንደ ፀሐይ ገላዋ እንደ እሳት ሲያበራ
ትሙት ብለው ማየ ዘለፋን ቢያጠጧት

እንደገና ብርሃን መሆኑ ባሰባት
ያንን ግሩም ያንን ደስ የሚል መዓዛ

በንጽሕና ያለ ሩካቤ ፀንሳ /አርግዛ/
ወለደችው በቤተልሔም ተጉዛ

ምጥ የለባት በመልአክ እጅ ተይዛ
የታደለች የተባረከች ፍጥረት

የበላውን ሰባ ስምንቱን ነፍሳት
አስገባችው በጥርኝ ውሃ ገነት

ከአድማስ አድማስ ወረቀት ቢሆን መሬት
ቀለም ቢሆን የሦስት ወር ውሃ ክረምት

ብዕር ቢሆን የዚህ ዓለም ሁሉ ዕፅዋት
ቢጻፍ አያልቅ የተአምርሽ ብዛት

ንግበር ብሎ ገና ሲፈጥረን ከጥንት
ፈጥር ሰጠን ድንግል ሕሊና ትሁት

በእርስዋ ሰበብ እንገባለን ገነት
ተመልከቱ የእግዚአብሔርን ምሕረት

ብንወርድበት መቼ ይወዳን ከእሳት
እኛ ግና በኃጢአታችን ብዛት

እንወድቃለን ከዚያ ጨለም ክርፋት
አደራሽን ቤዛዊት ዓለም ብፅዕት

በማልቀስሽ በመጨለቅሽ ብዛት
ሑሩ ሲለን እንድታወጪን ከእሳት

ቃል ኪዳንሽ እጅግ ታላቅ ነው ከጥንት
አንቺን አምኖ እንዴት ይጎዳል ፍጥረት

ማኅደሩ የአምላክ ሰማይ እናት
ታይቶ አይጠገብ ሁልጊዜ የልጅሽ ምሕረት

እኛን በቀኝ እንድታቆሚን ያን ዕለት
ለዓለም እስከ ዘላለም ዓለም

## ስለ ምሥጢረ ሆሣዕና

በስመ አብ  ብለን እስኪ ሰላምታ እናድርስ
ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ

እስኪ እናድታውስ የሆሣዕናን ትዕይንት
የሆነውን የነበረውን ያን ዕለት

ፋሲካቸው በስምንት ቀን ሲሆን
ከፋሲካ በሚቀድመው ሰሞን

ዘካርያስ የሚባል ነቢይ ካህን
ደስ ይበልሽ ኢየሩሣሌም ጽዮን

ንጉሥሽ ይመጣልና አሁን
በአህያ ላይ እንደ አንድ ደሃ ምስኪን

እንዲህ ብሎ የተናገረው ቃሉን
ለመፈፀም በአህያ ሆኖ መድኅን

ሲመጣ አይታ እርሱ መሆኑን ለይታ
ሀገሪቱ ተቀበለችው በእልልታ

በመንገዱም ቅጠሉን ቆርጠው በእርጥቡ
ልብሳቸውን ያነጠፉ አሉ ከሕዝብ

ሁለተኛም ዳዊት ልበ አምላክ ነውና
ሲዘምር እያስማማ በበገና

አስቀድሞ ይህችን ዕለት አየና
ሲሰብክልን የዚህች ዕለትን ዜና

አዘጋጀ ከህፃናት አፍ ምስጋና
ያለው ትንቢት መፈፀሚያ ቀን ናትና

እንዲህ ሆኖ ከቤተ መቅደስ ሲገባ
ሕፃናት እየወረዱ ከጀርባ

በጣታቸው እየጨበቱ ዘንባባ
በእግዚአብሔር የሚመጣው አምላክ

ብሩክ ነህ ለዘለዓለም ብሩክ
የዳዊት ልጅ መድኃኒት የሆንክ ለሁሉ

ሆሣዕና መባል ተገባህ እያሉ
በደስታ በፊት  በፊቱ ዘለሉ

ይህን ሰምተው ፈሪሣውያን ጸሐፍት
ቢናደድ ቢመላባቸው ቅንዓት

ሕፃናቱን ተው በላቸው አሉት
እንዲህ አለ ሲመልስላቸው ጌታ

ከጠላችሁ የሕፃናቱን ዕልልታ
ድንጋዮቹ የሚገባቸው ዝምታ

ያመስግኑ በእናንተ በሰዎች ፈንታ
በዚህ ጊዜ አምላክነቱን ሲገልጡ

ድንጋዮቹ በፊት ለፊቱ እየሮጡ
እንደ ሰዎች የምሥጋና ድምጽ ሰጡ

ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

## አባ ግራኝ ሞተ
## /ስለ አፄ ቴዎድሮስ/

**23 1515 1555 11 31132**
**23 1531 113 242 45**
**አዝ 4231 1131 242**

አባ ግራኝ ሞተ የሆዴ ወዳጅ /፪/
የሚያበላኝ ጮማ የሚያጠጣኝ ጠጅ

*እኔ መዩ ቱርክ ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ*

ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሳ ብሎ ስም
ዐርብ ዐርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም

ሺህ ገመር ሺህ ሺህ ጎራች የሸዋ ፈረስ
አንድ ጥርኝ ሆነ ቢዘልቅ ቴዎድሮስ

ፈረሱ አባ ታጠቅ ስሙ ቴዎድሮስ
ጠላት የሚበትን እንደዐውሎ ንፍስ

መቅደላ አፋፍ ላይ ጨኸት በረከተ
የሴቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ

መቅደላ መቅደላ አንቺ ክፉ ጎራ
ሴቱን ሁሉ ንቆ ሲኮራ ሲኮራ
ወንድ አንቺን ወደደ ተኛ ካንቺ ጋራ

አያችሁት ወይ ያንበሳውን ሞት
በሰው እጅ መሞትን ነውር አድርጎት
እርሳሱን እንደጠጅ ጎርሶ ሲጠጣት

አውሮፓም ያውቁሃል አፍሪካም ያውቁሃል እስያም ያውቁሃል
እንኳን የሰው ንጉሥ ውሃ  እንኳን ፈርቶሃል

አባትና እናቱ ያለአንድ አልወለዱ
አባ ታጠቅ ካሳ ያ ወንዱ ያ ወንዱ

የትግሬንም ንጉሥ ሲንቁ ሲንቁ
የሸዋንም ንጉሥ ሲንቁ ሲንቁ
ወንድ ያለ ራስዎ ገድለውም አያውቁ

ገድልን እንዳይሉ ሞተው አገኙዋቸው
ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በእጃቸው
ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው
ለወሬ አይመቹም ተንኮለኞች ናቸው

እንደ አፄ ቴዎድሮስ አላየሁም ኩሩ
ቢመጡ እንግሊዞች ምክር ሊማከሩ
በአርምሞ ሸኙዋቸው ሳያነጋግሩ

## ሰላም ለማርያም

**23 1555 1555 11 31132**
**23 1531 113 242 45**
**አዝ 4231 1131 113 242**

ሰላም ለማርያም የአምላክ እናት
የአቤል የዋሀት የአዳም ሕይወት

*እመቤቴ በምልጃሽ መድኃኒቴ ነሽ*

የአብ ቃል መቅረጫ ጽላቱ ለሙሴ
የመንፈስ ቅዱስ ቤት እመቃል ሞገሴ

የርኅራኄ መዝገብ እህተ መላእክት
የጻድቃን ተስፋቸው ጽላተ መለኮት

ትናንትን ተጨንቀን በጨለማው ዓለም
ዛሬ ብርሃን አየን በድንግል ማርያም

የኢያቄም ዕንቁ የሐና ንብረቷ
ሥጋ ነፍሴን እርጂያት ይቅርላት ቅጣቷ

በወንጌል ሰማነው ድንግል የአንቺን ዜና
አማላጅነትሽ ሲገለጽ በቃና

ከዳዊትም ሰማን ድንግል ስለአንቺ ክብር
ወትቀውም ንግስት እያለ ሲዘምር

በላዔ ሰብእ ከሞት ከሲኦል የዳነው
በምልጃሽ ነው እንጂ መች በጥርኝ ውሃ ነው

ሊውጡኝ ቢነሱ አጋንንት በሙሉ
ስምሽን ስጠራ ትቢያ ይሆናሉ

ጽዮን እመብርሃን ጽላተ ሥላሴ
የበረከት ካዝና ደመወዜና ዋሴ

ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ ሲከፋኝ ኑሮዬ
ድንግን አንቺ እኮ ነሽ አጽናኝ አለኝታዬ

ስምሽን ስጠራ ሲታወክ ሕይወቴ
አለሁልሽ በይኝ ድንግል እመቤቴ

ድንግል ሆይ አትርሽኝ የዘላለም ልብሴ
ምልጃሽ ያውጣኝ ከሞት ከክፉ ድምሳሴ

የቅዱሳን ካባ የቅዱሳን ኩታ
ጸጋ ሰማዕታት የድሆች አለኝታ

ሹመተ መሳፍንት ቅብዐ ለነገሥታት
የሰሎሞን ጥበብ የዳዊት መዝሙራት

ዓለም የዳነብሽ ከሞት ከሲኦል
ለእኔስ እናቴ ነሽ ማርያም ድንግል

አድኚኝ እናቴ ከሥጋ ፈተና
እኔማ ያለአንቺ አልችልም ልጸና

ሸክም የከበደኝ እንግልት ሆኖለሁ
ከኔ እንዳትለይ አደራ እልሻለሁ

አደራ እልሻለሁ ከጎኔ አትራቂ
ወዳጅ ዘመድ የለኝ ያለአንቺ ጠባቂ

ተሳክቶኝ ባየው ሐሳቤ ምኞቴ
ድንግል ያለአንቺማ መች ይጸናል ቤቴ

ልጅሽ እንዳይረሳኝ መንግሥተ ሰማያት
ከኃጢአት ጠብቆ እንዲያኖረኝ ገነት
አንቺ ንገሪልኝ ለዓለም መድኃኒት
ተስፋዬ ነሽና አትርሽኝ የእኔ እናት

## እግዚአብሔርም

እግዚአብሔርም አዳም ባጠፋው ጥፋት
በተስፋ ቃል አጠናበተው ያን ለት

ለአዳም በገባለት ቃል ኪዳን
አምስት ሺ ከአምስት መቶ ዘመን

ሲፈፀም ያ የተስፋ ቃል ደረሰ
የአዳም የስቃይ ዘመን ፈረሰ

አዳምም በሲኦል ሲኖር ተቀብሮ
አዳነው ሞቱን በሞቱ ቀይሮ

አምላክም ወደዚህ ዓለም ሲመጣ
ቆየችው እመቤታችን ተምርጣ

የሌለባት መርገመ ፍዳ ከጥንት
ጸነሰችው በመልአኩ ቃል ብስራት

ፍቅር ስቦት ወደዚህ ኧለም መጣና
ለአዳም ምን ያልሆነለት አለና

ተወለደና ድንግልናዋን ሳይሽር
ለሰው ልጅ ሲል ተመላለሠ በምድር

በዮርዳኖስ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ
በዲያብሎስ የተጻፈውን ተራምዶ

አጠፋለት ያንን ደብዳቤ ዳምስፎ
ከባርነት የሚያልቅቀው ጨርሶ

በመስቀል ላይ በዕለተ ዓርብ ተወግቶ
ከሲኦል በደሙ አነፃው አውጥቶ

እንዲህ አድርጎ ወደ ጥንት ቦታው መለሰው
በምህረቱ ዳግም ገነትን አሣየው

በአባታችን በአዳም ጥፋት በደል
ገብተን ነበር እኛ ሁላችን ሲኦል

በስራችን በኃጢአታችን እኛማ
ሆነን ነበር ከመርገም ግዞት ጨለማ

ግን አዳነው የፍቅር አምላክ ነውና
በትህትና እናቅርብለት ምስጋና

ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

## አስቀድሞ

አስቀድሞ ነፍስ ሳትወጣ በፊት
እናቱን ቆማ ስታለቅስ ቢያያት

ለዮሐንስ አደራ ብሎ ሰጣት
ይርዳሽ ያፅናሽ ይህ ልጅሽ ነው አላት

እርሱንም ቆሞ ሲያለቅስ ብያየው
ቢወደው ለእናቱ አደራ ሰጠው

ዮሐንስም እያለቀሰ በሞቱ
እናቱን አኖራት ወስዶ ከቤቱ

ሊፈፀም የተናገራው ዳዊት
አይሁድ ጌታን ውሃ ጠማኝ ሲል ሰሙት

ኮምጣጣውን ውሃ ቀላቅለው ሰጡት
ቀመሰና ያን የሰጡትን ሐሞት

ተፈፀመ ትንቢቱ ሁሉ አሁን
ይህን ብሎ ዘለፍ አድርጎ ራሱን

በሥልጣኑ ከሥጋው ለያት ነፍሱን
በነፍስ ወርዶ ነፍሳት ካሉበት አዘቅት

ነፍሳትን የወረዱትን ከጥንት
ከዚያ አውጥቶ ወስዶ አገናቸው ገነት

ተጠራጥሮ አንድ ሐራዊ ሞቱን
ሞተ ብሎ በጦር ቢወጋው ጎኑን

አፈሰሰ ከውሃ ጋራ ደሙን
አይሁድም እርግጥ መሞቱን አውቀው

ሳያዝኑለት ነገ ሰንበት ነው በለው
አይደር አሉ ከመስቀል ይውረድ ሥጋው

ኑቅዲሞስ ቀድሞ በሌሊት ያየው
ዮሴፍም በአርማትያስ ያላት

ሞት ሳይፈሩ ከጲላጦስ ፊት ቆመው
ተካሰሱ በድኑን እናውርድ በለው

ጲላጦስ ጠዋት ስላየው ታግሶ
ትዕግስቱን ጻድቅነቱን አስታውሶ

እንዴት ሞተ ብሎ ጠየቀ መላልሶ
ሞተ ቢሉት እጅግ አዘነ ተከዘ

በድኑን ስጡ ብሎ ጭፍሮቹን አዘዘ
ከመስቀሉ አወረዱና ሁለቱ

ገነዙና በድርብ በፍታ በሽቱ
ከተክል ውስጥ ከአዲስ መቃብር ቀብረውት

መቃብሩን በታላቅ ድንጋይ ገጠሙት
ወልድ ጌታ በተናገረው መሠረት

ተነሣና ህቱም መቃብር ሳይከፍት
ለማርያም ወዶ ተገልጦ ታያት

ረቢ ብትል አይዞሽ ጠንክሪ አላት
እንዲህ ሆኖ ሞቶ ተነስቶ በፍጥነት

አዳምን አገባው ከተድላ ገነት
የአዳም ልጆች አሁን ያላችሁ በመሬት

አመስግኑት ስላወጣችሁ ከእሳት
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

ለዘለዓለም ምሥጋናህ ይብዛ ክርስቶስ
ለዓለም ወለዓለም ዓለም አሜን

## እመቤቴ

እመቤቴ የፍጥረት ሁሉ አለኝታ
ክብር ለስምሽ ይገባል ላንቺ ሰላምታ

እናታችን አማላጃችን ድንግል
ተስፋችን ነሽ የጽድቅ የብርሃን አክሊል

ማርያም ሆይ አንቺ የገነት መውረሻ
እንኳን ለሰው የምትራሪ ነሽ ለውሻ

ባንቺ ምልጃ ባንቺ ልመና ያመኑ
በኪዳንሽ በልጅሽ አምነው የጸኑ

ለክብር በቁ ከዳግመኛ ሞትም ዳኑ
ኑሮው ከፍቶት ድሃ ሲጨነቅ ከቤቱ

አይዞህ ብለሽ የምታጽናኚው እናቱ
ሲራብ ጉርሱ ሲዝል ሲደክም ብርታቱ

አንቺ እኮ ነሽ ለችግረኛ ሕይወቱ
ምጽዋት ሰጥተው ስለ ቅዱሱ ስምሽ

ሲደሰቱ ምዕመናን በውል ምልጃሽ
ተለይቼ እንዳልቀር ምስኪን ልጅሽ

ከጌታዬ አማልጂኝ ድንግል እባክሽ
ታውኮብኝ በዓለም ጣጣ ሕይወቴ

ስፍገመገም እጅግ ጠንቶብኝ ጉዳቴ
ታድኝን ዘንድ ከሥጋ ወጥመድ ጭንቀቴ

ድረሽልኝ ድንግል ማርያም እናቴ
ሃይማኖቴ ቢታይ ቢመዘን ምግባሬ

ስለሚበልጥ ከክብሬ ይልቅ ነውሬ
በሠንሠለት እጅና እግሬን ታስሬ

በገሃነም ይበዛልና አሣሬ
በምልጃሽ አሁን አድኝን ዛሬ

## ማን ይመራማር

**3 1 5 5 1 5   4 5  1 3 1   1 3   1 5 5 5 1 3   2 4 2  /፪/**
**3 1 1 1 3   2 4 2   3 1 1 1 3   2 4 2   4 2 2 2   2 2   42**

ማን ይመራማር /፪/
ያንተን ሥራ ያንተን ክብር ማን ይመራማር

አዳምና ሔዋን  ጠፍቷቸው መንገዱ /፪/
ለሰው ልጅ መከራ ትተውለት ሄዱ

እስከዚያው ድረስ ነው ሲሶ ማረሳችን /፪/
እንገባው የለም ወይ በየመሬታችን

እግዚአብሔር ምን ይበል እኛ ቅጥ ብናጣ /፪/
በስምንተኛው ሺ በቀጠሮ መጣ

አዳም በበደለው ጌታ ለዓለም ክሶ /፪/
ቆሟል ቀራኒዮ ከሜዳ ለብሶ

አለህም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል
የለህም እንዳልል ያመሻል ይነጋል

እባክህ አምላኬ አትመራመረኝ /፪/
እንደ በላኤ ሰብእ በጥቂት ነገር ማረኝ

አንተነህ ይላሉ የዓለም ሁሉ ጌታ
ሰማይና ምድር ያቆምከ ያለዋልታ

ወዴት እንዴት ይሆን ያለህበት ቦታ
እነግርህ ነበረ እኔ በቆይታ

የሰራችልኝን የእናትህን ወሮታ

ሁልጊዜ አትለይም እርሷ ከእኔ እርዳታ
ምግብና መጠጤን በውል አዘጋጅታ

እግሬን አሳጥባ ዙፋን አዘርግታ
ትከተለኛለች ለእርሷ ልዕልና

ለእርሷ ልዕልና የለውም ቅሬታ
ልጇ ፍፁም ንጉሥ የለው ባለፋንታ

እኔስ ይገርመኛል ከጠዋት እስከ ማታ
ካለሁበት ሀገር አለመለየቷ

ለሁሉ ነው እርሷ ይህ ሩህሩህነቷ
ከቶ አይፈፀም ይህ መልካምነቷ

አንቺ አማልጂን እንጂ መድኃኒት ለዓለሙ
ወልደ አብ ሲለምን አባ ስረይሎሙ

እመቤት እመቤት የዓለም መድኃኒት
እንድታማልጂኝ በዕለተ ምጽአት

ምንም ከፋ ብንሆን አውቀን ብናጠፋ
አዛኝቷ አስምሪን እናት አትገፋ

ንኡ ና ሑሩ ሲል ሲያደራጅ ልጅሽ
እንደ በላኤሰብእ ያድነን ጥላሽ

እባክህ አምላኬ አትመራመረኝ /፪/
እንደ በላኤ ሰብእ በጥቂት ነገር ማረኝ

ያንተን ሥራ ያንተን ግብር ማን ይመራመር

## ርግብና ዋኔን

4 4 4 4 5 5 3 1 1 5 4 2
4 4 4 5 2 5 3 1 1 5 4 2
3 3 1 1 3 3 4 2 3 1 4 2
3 3 1 1 3 3 4 2 2 4 2

*ርግብና ዋኔን አብረው ዘመቱና*
*ርግብ ደህና ገባች ዋኔን ገደሉና*

እስቲ በስመ አብ ብዬ ልቀኝ ለእመቤቴ
ማርያም በመሆኗ ክብሬና ሕይወቴ

ሰላም እልሻለሁ ጽላተ ጽዮን
ደጅ እጠናሻለሁ አምኜ አንቺን

አዛኝቷ እመቤት ኪዳነ ምህረት
አለሁልህ/ሽ/ ብለ/ሽ/ አውጪኝ ከመዓት

እስቲ ሁላችሁም ኪዳነ ምህረት በሉ
መድኃኒት ናትና ለሰው ልጆች ሁሉ

ሁሌ እጠራሻለሁ በቃል ኪዳንሽ
የምህረት አማላጅ ድንግል አንቺ ነሽ

የዓለም ፈርጥ አንቺ ነሽ ማርያም እመቤቴ
እመካብሻለሁ እስከ ጊዜ ሞቴ

ያንን የእሳት ባሕር አሻግሪኝ ድንግል
እንዳልወድቅ አደራ ከሲኦል ገደል

የነቢያት ትንቢት የሰማዕታት አክሊል
ያላንቺ ማን አለኝ እመቤቴ ድንግል

ያዕቆብ በህልሙ ያየት መሰላል
የዓለም አስታራቂ አንቺ ነሽ ድንግል

ታማልደናለች እጆቿን ዘርግታ
ከቶ ዕረፍት የላትም ከጧት እስከ ማታ

ኪዳነምሕረት ነሽ አንቺ የኛ ተስፋ
መርቆ የሰጠን አልፋና ኦሜጋ

የዓለም ሁሉ መቅረዝ መንበረ ሥላሴ
መድኃኒት እሷ ነች ለሥጋም ለነፍሴ
ሁሌ ላመስግናት ተፈታ ምላሴ

የምሕረት ቃል ኪዳን የሰው ልጅ መዳኛ
እንድታማልደን የተሰጠች ለእኛ

ምላሴ ተናገር የማርያምን ዝና
ለኛ መሰጠቷን ሳትፈጠር ገና

ታስባ ስትኖር በእግዚአብሔር ሕሊና
ተወልዳ አደገች ጊዜው ደረሰና

ዘመን የማይሽረው ስላላት ቃልኪዳን
ታማልደናለች መድኃኒት በመሆን

ምን ቃላት ይገኛል እሷን ማመስገኛ
እነ ሕርያቆስ ያልቻሉት እነኛ

ከዓይኗ እያዘነበች የዕንባዋን ዘለላ
ወደ ግብፅ ወረደች አንድ ልጇን አዝላ

ፅጌ ፀዐዳ ነች እመቤቴ ድንግል
ድረሽልን ሲሏት ከተፍ ነው የምትል

የፃድቃን እመቤት የኃጥአን ተስፋ
ወዳንቺ እጮኻለሁ ሳዝንና ስከፋ

በላኤሰብን ያዳንሺው ድንግል
ለእኔም አትንፈጊኝ ይህንን ዕድል

ስንቅ የለኝ ለነፍሴ እንዴት ልሆን ነው
ድንግል እመቤቴ መግቢኝ አንቺው

ጥላሽን ጣይብኝ ኪዳነ ምሕረት
ስጨነቅ ስጠበብ ስጋለጥ ያን ዕለት

ድንግል መድኃኒት ነሽ የሰው ልጆች ተስፋ
ከጎኔ ቁሚልኝ ሳዝንና ስከፋ

የዓለም መድኃኒት ነሽ ማርያም እመቤቴ
በረድኤት ግቢልኝ ነይልኝ ከቤቴ

አደራሽን ማርያም ኪዳነ ምሕረት
ፀጋሽን አልብሺኝ ኋላ ስራቆት

ዕርቃኔን መሆኔን አውቀዋለሁና
አልብሺኝ ፀጋሽን በኢያቄም በሃና

እስቲ ሁላችሁም ኪዳነ ምሕረት በሉ
መድኃኒት ናትና ለሰው ልጆች ሁሉ

አፍሮ አይመለስም የቆመ ከደጇ
እመቤቴ ማርያም የጭንቅ አማላጇ

የአዳም መድኃኒት አንቺ ነሽ ድንግል
በኢያቄም በሃና አውጪኝ ከሲኦል

አንቺ የኤዶም ገነት የሰው ልጆች ተስፋ
መድኃኒት ነሽና አዝኖ ለተከፋ

የዓለምን መድኃኒት በጀርባሽ አዝለሽ
ኧረ ለምን ይሆን ቁራሽ የለመንሽ

ፍግም ብዬ ልስገድ ለእመቤቴ ድንግል
እርሷ በመሆኗ የሰው ልጆች ዕድል

## አቤቱ ደግ ሰው አልቋልና

**5 2 1 115 1113 4 2 2 2 4 2**
**5 2 1 115 1113 4 2 2 3 2 3**
**3 5 2 4 4 5 3 1113 4 2 2 2 4 2 /፪/**

*አቤቱ ደግ ሰው አልቋልና /፪/*
*ከምድርም ፍቅር ጠፍቷልና /፪/*
*እንደ ቸርነትህ አድነን /፪/*
*በደላችንንም አትቁጠር*

የረድኤት አምላክ ፍቅርን ስጠን /፪/
እንደ አህዛብ አታድርገን /፪/
ክርስቲያን ነንና እንዋደድ /፪/
እባክህ አንውጣ ካንተ መንገድ /፪/
አቤቱ ንፁህ ልብ ፍጠርልን /፪/
ሰውን የሚያስወድድ ያለ እንከን /፪/
አንደበታችን እንዲናገር /፪/
ስለ ሰላም ቋንቋ ስለፍቅር /፪/

በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመራ /፪/
ትሩፋት ደግነት የሚሠራ /፪/
አንደበቱ ሁሉ የታረመ /፪/
ለቃለ ወንጌሉ የደከመ /፪/
ምግባርና እውነት የተሰጠው /፪/
እባክህ አድለን ሁነኛ ሰው /፪/
አንተን የሚመስል በሕይወቱ /፪/
ፍቅርና ትህትና የግል ሀብቱ /፪/

የማስመሰል ፍቅር እየበዛ /፪/
ሰው ረክሷልና እንደዋዛ /፪/
ፍፁም መዋደድን ስጠንና /፪/
አዲስ ሰው እንሁን እንደገና /፪/
ደገኛ ሰው ማግኘት አስቸግሯል /፪/
እስከ መጨረሻው ማን ይፀናል /፪/
ምግባሩ ትክክል እውነተኛ /፪/
ልቡ የሚፀየፍ ከዳተኛ /፪/

## ኢትዮጵያ ሆይ ተነሺ

**2 1 3 2 4 5 5 2 4 2 4 2 1 1 1 5 5 3 2 3**
**2 1 3 2 4 5 5 2 4 2 3 4 2 2 2 2 4 2** } **/፪/**

**1 5 1 1 3 4 2 4 2 4 2 1 1 1 5 5 3 2 3**
**1 5 1 1 3 4 2 4 2 4 5 2 2 2 2 4 2** } **/፪/**

*ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ ክብርንም ልበሽ*
*በአዲስ ምሥጋና ይመላ ልብሽ*
*የተወደደ ነው በእግዚአብሔር ሕዝብሽ /፪/*

ንብረቱ ጠፊ ነው ከንቱ የማይረባ
በግፍና ቅሚያ በአመፅ ሲገነባ
ሲሳይሽ ብዙ ነው ከአምላክ የተሰጠሽ
በረከት ለማግኘት መሥራት ነው ጠንክረሽ

የአሕዛብ ብልፅግና አያስቀናሽ ፍፁም
ኃላፊ ጠፊ ነው ምኞቱም ዓለሙም
ደመና ነውና ይበናል በቅጽበት
በግፍ የተገኘ የተከማቸ ሀብት

ይልቅ በቅንነት በሰላም ለሰራ
ሲሣዩ ብዙ ነው ክብሩም አያባራ
ጉቦና ፍትሕን ማጣመም እንዳንለምድ
ከወንጌሉ ጋራ አለብን መዛመድ

እግዚአብሔር ያለው ሰው በእርሱ የታመነ
ከግፍ ሥራ ሕመም አካላቱ ዳነ
ክርስቲያን ነኝ ብሎ ጉቦ የሚበላ
የሚያቃጥል እሳት ያገኘዋል ኋል

በመታመን ፀጋ ይጠራ ስማችን
እውነተኛ እንሁን ለውድ ሀገራችን
የራሱን ሳይሻ ለሀገር የሚያስብ ሰው
በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ነው

## የብርሃን እናት ነሽና

*የብርሃን እናት ነሽና የብርሃን እናት*
*ለምኚልን ድንግል ለምኚልን /፪/*

ፀጋንና ክብርን የተመልሽ
ከሴቶች መካከል የተመረጥሽ
ለቃሉ ማደሪያ ዙፋን ሆነሽ
በደመና መንበር የተመሰልሽ

የሽቶ መኖሪያ የተቀደስሽ
መዓዛሽ ያማረ ሽቶ ያለሽ
ውዳሴሽ ብዙ ነው እናታችን
ስምሽን እያሰብን መጽናኛችን

በሀሳብ በግብር ፍፁም ሆነሽ
ምንኛ ብሩህ ነው ድንግል ልብስሽ
አንቺን የሚመስል የለምና
ይሰማል ምልጃሽ ያንቺ ልመና

የብርሃን መውጫ ምሥራቁ ነሽ
ሰውን ለለወጠ ድልድይ ነሽ
ምሥጋናሽ አያልቅም ለዘላለም
ማህሌት ነሽና በአርያም

መላእክት ፈጥረትሽን ያደንቃሉ
ጌታን በመውለድሽ ይመካሉ
ሰማይና ምድር ሳይወስኑት
ባንቺ ተወሰነ እፁብ በእውነት

የሽቶ መኖሪያ የተቀደስሽ
መዓዛሽ ያማረ ሽቶ ያለሽ
ውዳሴሽ ብዙ ነው እናታችን
ስምሽን እያሰብን መጽናኛችን

## አልፈድም እኔ

*አልፈድም እኔ በማንም በደል በማንም ኃጢአት*
*በፈረደኩት እንዳልመዘን ጌታ ሲመጣ በ ኃይል በሥልጣን*

በቸርነቱ አምላክ ባይተወው በደሌን ሁሉ
ውስጤ ቢፈተሽ በተሰጠኝ ሕግ በቅዱስ ቃሉ
በምን ምግባሬ በሰው እፈርዳለሁ ዐይኔን አቅንቼ
በደሌ በዝቶ ለራሴ ሳላውቅ በኃጢአት ሞቼ

ይልቅ የአንዱን ሸክም ሌላው ሰው አዝሎ መጓዝ ይሻላል
መፍረድ ከመጣ አንድም ሰው አይድንም ሁሉም በድሏል
ወንድም ወንድሙም እየከሰሰ ለፍርድ አቁሞ
አሕዛብ ያያል በንትርኩ እጅግ ተገርሞ

ክርስቲያን ሆኖ ከወንድሙ ጋር እየተጣላ
ዓለም ዳኞችን በፀብ ፍርድ ቤት ታረቁ ብላ
ክርስቲያን ሆነን በአሕዛብ መሀል እየተካሰስን
አምላክ አዘነ የመስቀሉን ዓላማ ስተን

መቼ ከሰሰ የከሰሱትን የገረፉትን
አይተናል ሲምር ለጠላቶቹ ምህረት ሲለምን
ለጽድቅ ሥራ ለእውነት ብለን መጥተናል እንጂ
ማነው የሾመን በወንድሞች ላይ አድርጎ ፈራጅ

## የአብርሃም አምላክ

5 2 2 2 3 4  2  5 1  5 3 5 4 5 5  /፪/

2 5 2 3 1  5 1 3  1  2 4  2  5 2 3 2

የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም ቤዛ
ወገኖቹን ሁሉ በራሱ ደም ገዛ

የሐሰት ምስክር አቁመው ከሰሱት
በሞት እንዲቀጣ ሁሉም ፈረዱበት

ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ

በብርሃን ዙፋን ላይ የቆሙት እግሮቹ
በችንካር ላይ ቆሙ ምንም ሳይሰለቹ

የብርሃን አክሊልን ለሰማዕት ያደለ
በእሾህ አክሉል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ

## ኑ እንቅረብ

1 1  2 3  4  3 4 2  3 5 5  5

1 1  2 3  4  3 4 2  2 2 2  2

2 1 1  5  1 3  2  2  2 1 1  5 1 3 3  3

3 1 1  5 1 2  3 4 2  2 2 2  2  /፪/

1 1 1 3 2 1  1  4 4 4 5 1 5  5

3 3 3 2 4 2  4  2 3 4 2 2 2  2

*ኑ እንቅረብ መጠራት ሳይመጣ /፪/*
*ሥጋውን እንብላ /፫/ ደሙንም እንጠጣ*

የቀራንዮ በግ የአምላክ ሥጋው
ተሰውቶልናል እንመገበው
እድፉን ኃጢአታችን በንስሐ አንፅተን
እንቀበል አምነን በልጅነታችን
መቅረብ ወደ ጌታ በእምነት የሚገባው
በስተርጅና አይደለም በወጣትነት ነው

ጨረቃና ፀሐይ ደም የለበሱለት
ከዋክብት ከሰማይ የተነጠፉለት
ይኸው ተፈተተ እሳተ መለኮት

ቅድስት እናታችን ቤተክርስቲያን
ትጋብዘናለች ሥጋና ደሙን
የአማኑኤል ሥጋ ይኸው ተዘጋጀ
ከግብዣው ተጠራን አዋጁም ታወጀ

መጥቁ ተደወለ እንቅረብ በእልልታ
በኋላ አይረባንም ዋይታና ጫጫታ
ይህችን ዕድል ፈጥነን እንጠቀምባት
ዓለምን አልያዝንም ብዙ ልንቆይባት

ከአሁኑ ቅረብ ታውጇል አዋጁ
የይለፍ ደብዳቤ ስንቅን አዘጋጁ
ይህ ዓለም ጠፊ ነው በሀብት አትመኩ
ብሏል አምላካችን ተስፋችሁን እንኩ

## ስለ ቸርነትህ

2 3 1 5 4 2  3  4 5  1 3  4 2  2  /፪/ - አዝ

2 3 1 5 4 2  3  2 3  1 5  1 5  5  - ዘማች

*ስለ ቸርነትህ ጌታ ተመስገን*
*ስለ ፍፁም ፍቅርህ አምላክ ተመስገን*

ማነው የገመተው ከዛሬ መድረስን
ልብሱ ሳይነዳ በእሳቱ ወላፈን
ባህሩን አሻግሮ ማዕበል አቁሞ
እርሱ ያውቅልናል ለመጪው ቀን ደግሞ

ሃሌ ሃሌ ሉያ መስዋዕት እናቅርብ
ጌታ ይገልጋል የተሰበረ ልብ
ክርስቶስ ከሌለው ፍቅር ላይኖረው
ሰላም ሰላም ይላል ፍጥረታዊው ሰው
ሰላም ሰላም ይላል የዘመኑ ሰው

የኢየሱስ ነገር ለሚጠፉት ሁሉ
የመስቀሉ ነገር ለሚጠፉት ሁሉ
ሞኝነት መስሏቸው ክህደት ተሞሉ
የስንፍና አመል እያናወዛቸው
መጾም መጸለዩ ይጎዳናል ብለው
አምላክን ቢክዱ ፍቅርን ነፈጋቸው

## በህይወቴ

2 3  4 2  2  1 4  1 5  5

1 5  1 1 2 3 1  1  2 2 2 3  4 2  2

2 2 2 3  4 2  2  1 4 1 5  4 2  2
2 2 2 3  4 2  2  2  3 1 5  1 1 2 3 1  } /፪/

*በህይወቴ በዘመኔ ደስ የሚለኝ ለእኔ በወንጌል ማመኔ /፪/*

ሕይወቴ ቢመራ ጌታ በቃልህ
ጣፋጭ ይሆን ነበር ቢያድሰኝ ፍቅርህ
ያንተ ፀጋ ጌታ ስለበዛልኝ
ጨለማው ተገፎ ብርሃንህ መራኝ

ወዴት እሄዳለሁ የእጅህ ጥበብ ሆኜ
ፍቅርህ እያደሰኝ ሞተህልኝ ድኜ
ምን አይነት መውደድ ነው አንተ ለእኔ ያለህ
ምን ይከፈለዋል ለፍፁሙ ፍቅርህ

ምን አይነት መውደድ ነው አንተ ለእኔ ያለህ
ምን ይከፈለዋል ለፍፁሙ ፍቅርህ
ደጅህ ላይ ተጥዬ ደጅህ ላይ ልሙት
ቃልህን ልጠብቅ በፍፁም ፍርሃት

## መጾሙን ይጾማል

**15 1515 151515 151551 42**
**(52 45 11 42)**
**23 1551 11 23 42 2**
**23 2325 4 13 54444 2**
**45131542**

*መጾሙን ይጾማል ሁሉም የአዳም ልጅ /፪/*
*የጊዜውን መድረስ የሚያውቅ የለም እንጂ /፫/*
ይደርሳል ሰዓቱ *ሳሰብ ሌላ* /፪/
የተሰቀለውን *ሥራው* ሳልበላ /፫/
ድኋ ጾመ ድኋ ተሰቅሎ ከቤቴ /፪/
አወይ አለማወቅ ሳልማር መቅረቴ /፫/
ደግሜ ደግሜ *ቀረኝ አሌፋቱ* /፪/
አድኅነኒ ሣልል አትጥራኝ በከንቱ /፫/
እኔስ እሄዳለሁ አጣቢ ፍለጋ /፪/
በጣም አድፎብኛል የለበስኩት *ሥጋ* /፫/
ዳዊት እንዴት ይሙት *ሳንተዋወቀው* /፪/
የሚመጣውን ሁሉ በገና የሚያውቀው /፫/
ዐርብ ረብዕን ገደፍኩ በ*ሥጋ* በአዋዜ /፪/
እንዲህ ለሚደርሰው ለማይቆየው ጊዜ /፫/
ከ*ሥጋ*ው ሳልበላ *ተጠይፌ ደሙን* /፪/
ማን ይችለው ይሆን የላይ ቤት ረሃቡን /፫/
ከንብረቴ ሁሉ አል*ጋ*ዬ ነው ሀብቴ /፪/
አድርሶኝ ይመጣል ከዘላለም ቤቴ /፫/
ብልህ ነው ስትሉኝ *እዩት ምኝነቴ* /፪/
በራሴ ላይ ሆኖ አላውቀውም ሞቴን /፫/
መማሩንስ ዳዊት ተምሬ ነበረ /፪/
ከአምላኪየ ሳልደርስ ልቤ ሰንፎ ቀረ /፫/
እንኳን ነአኩተከ *በስመ አብም ቸገረኝ* /፪/
ዳዊት እንዴት ተማርከ እባክህ ንገረኝ /፫/

## የኛ ጌታ

*የኛ ጌታ የኛ መድኅን*
*በቸርነትህ ታደገን*
*እኛ እንደሆነ ኃይል የለን*

ጠዋት ለምልማ ማታ ጠፋች
የሰው ህሊና እያባባች
ዓለም ምኗ ነው የጣፈጠን
እያሳሳቀ የወሰደን

ዛሬ አለች ሲሏት ትጠፋለች
ከነተንኮሏ ዓለም ሟች ነች
እሾህ በቅሎባት እሾህ ሆኖ
በመተላለፍ ሰው ሊያልቅ ነው

ከእኛ ጋራ ያለው ኃያል ነው
በሥጋዊ ዓይን ባናየው
የጦሯ ብዛት መች አድኗት
ዓለምን ትምክህት ተዋህዷት

እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኛ
እንደ ሰው ንብረት ወደረኛ
እንደ ዓለም ጉልበት ጉልበተኛ
በአምላክ ፊት ሲታይ ሕመምተኛ

## ለእኔስ ልዩ ነሽ

**23342 2 42 423 15 13 31 31 /፪/**
**342 2 42 423 15 13 31 31**
**23342 2 42 423 15 13 31 31**
**23342 233 42 2 42**
**23342 2 42 423 15 13 31 31 /፫/**
**23342 233 42 2 42**

*ለእኔስ ልዩ ነች ድንግል ማርያም*
*ለእኔስ ልዩ ነች እመብርሃን*
*ፈልጌ /፪/ ላንቺ ምሥጋና አላገኘሁም /፪/*

ልቤ ሲያበቅል የኃጢአት አረም
ውስጤ ሲሸፍት አልተወችኝም
ከቤተ መቅደስ እጇን ዘርግታ
ትጠራኛለች የኔ መከታ

የሆዴን ሀዘን የልቤን ምሥጢር
እነግርሻለሁ አንድም ሳይቀር
የምትሸሽጊ የሕዝብን ኃጢአት
ለእኔስ ልዩ ነሽ ድንግል አዛኝት

ጣዕሙ ልዩ ነው ከእርሷ ጋር መኖር
ድንግል ይዤ መቼም አላፍር
ወደ ጽድቅ ሕይወት ትወስደኛለች
ድንግል ማርያም ለኔ እናቴኮ ነች

በሀዘን ስሰበር ማንን እጠራለሁ
ውስጤ ሲደማ ለማን እነግራለሁ
ከኃጢአት እድፍ ንፁህ መሆኛዬ
አንቺ ነሽ ድንግል የኔስ መጽናኛዬ

የኃጢአት ቁስል ያለአንቺ አይጠግም
ልጅሽ ሳይፈቅድ በህይወት አይኖርም
ከልጅሽ ሌላ መድህን የለኝም
ከፀሎት በቀር ፍፁም አልድንም

## ጽኑ ክርስቲያኖች

423 15 13 42 422 22 2 42
423 15 13 42 423 33 3 231
545 13 42 45 422 22 2 42

423 15 13 42 422 22 2 42
423 15 13 42 423 33 3 231
545 13 42 45 423 33 3 231
545 13 42 45 422 22 2 42

ፅኑ ክርስቲያኖች ልናችን አይውደቅ
የእግዚአብሔርን እቃ ጦሩን እንታጠቅ /፪/

ማዕበሉን አይቶ ልባችን አይፍራ
ታማኙ ጌታችን አለ ከእኛ ጋራ /፪/

ሰማዕታት ልጆቿ የዓለም ጣዕም ንቀው
ያላውያን ዛቻ ፈተናውን አልፈው
ርሃቡን ስደቱን መከራን ታግሰው
ለዚህ አድርሰዋታል ተዋሕዶን ጠብቀው።
ክህደቱ ቅሰጣው ኑፋቄው ቢነዛ
ሰይፉ ስለት ቢያፏጭ ፉከራው ቢበዛ
በድንግል ቃል ኪዳን መሠረቷ ጠብቋል
በቅዱሳን ፀሎት ቅጽሯ በእሳት ታጥሯል።

አዝ

ጥንተ ጠላታችን ፈተና እያስነሳ
ዙሪያችን ቢከብ ተርቦ እያገሳ
መከራን ቢያበዛ ስደት ቢያደርስብን
እስከ ሞት የሚያደርስ ስቃይ ቢያበዛብን
ዓለም ላቆመች ለጣኦት አንሰግድም
በመከራው ጽናት ሃይማኖት አንክድም
ከሚነደው እሳት አምላክ ያድነናል
ባያድነን እንኳን እሳቱን መርጠናል። ዳን. ፫

አዝ

እንደ ግያዝ አንሁን ታውሮ ዓይናችን
በእሳት ሰረገሎች ተከቧል ዙሪያችን
ሰይፍን የሚያነሱ በሰይፍ ይወድቃሉ
ከእኛ ጋራ ያሉት ከእነርሱ ይበልጣሉ።
የጠሉህን ውደድ በሚል ህያው ቃሉ
ሲያሳድዱህ ጸልይ በሚል ክቡር ቃሉ
በመንፈሳዊው ፍቅር ይጠንክር ልባችን
ይህን ነው ያዘዘን ቅ ዱስ አምላካችን

አዝ

ነቅተን ከታጠቅን የጽድቅን ጥሩር
በትጋት ከቆምን በእምነት በፍቅር
በጾም ጸሎት ስግደት ምጽዋት
በንስሐ ጸድተን ከጸናን በእውነት
በሥጋ ወደሙ በጸጋው ከታተምን
በህይወትም በሞት ከእርሱ ጋር ህያው ነን።
በወደደን በእርሱ ከሁሉ እንበልጣለን
በወደደን በእርሱ አሸናፊዎች ነን።

አዝ

ንፋስ ማዕበሉ የማይነቀንቀው
መሰረቷ ጽኑ ቅጽሯም ጠንካራ ነው
የገሃነም ደጆች አይችሏትምና
ጸንታ ትኳዛለች ተዋሕዶ ገና
ፅኑ ክርስቲያኖች ልናችን አይውደቅ
የእግዚአብሔርን እቃ ጦሩን እንታጠቅ
ማዕበሉን አይቶ ልባችን አይፍራ
ታማኙ ጌታችን አለ ከእኛ ጋራ